# የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር

## የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ማመልከቻዎችን

## ለማስተናገድ የተዘጋጀ የወስጥ አሠራር መመሪያ

## ቁጥር 272/2013

መጋቢት 2011 ዓ.ም

## 1.መግቢያ

የመንግሥትና የሕዝብ የሆነው የማዕድን ሀብት በአካባቢና በኅብረተሰቡ ላይ ጉዳት ሳያደርስና የኅብረተሰቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማዕከል በማድረግ በዘላቂ የልማት መርህ የበለጠ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊሰጥ በሚችል መልክ መልማት እንዲችል እና ለፈቃድ ጠያቂዎች ፈጣን፣ ጥራት ያለው እና ፍትሐዊ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል፤

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚሰጡ ፈቃዶች በማዕድን ሕግ መሠረት አመልካቾች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸውን፣ ለሀገር የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ለማረጋገጥና ጥያቄዎቹ በአግባቡ እየተገመገሙ የመጡ ስለመሆናቸው በማጣራት ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ በማስፈለጉ፤

የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ አሠጣጥን የሚያጣራ የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ግምገማ ውጤት አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ማመልከቻዎችን ለማስተናገድ ይህ የወስጥ አሠራር መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ይህ መመሪያ የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ማመልከቻዎችን ለማስተናገድ የተዘጋጀ የውስጥ አሠራር መመሪያ ቁ. 272/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

1. በማዕድን ሥራዎች ዐዋጅ ቁጥር 678/2002 (በዐዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሻሻለው) እና በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 አንቀጽ 2 የተደነገጉት ትርጓሜዎች ለዚህም የውስጥ አሰራር መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
2. "የማዕድን ሕግ" ማለት እንደ አግባቡ የማዕድን ሥራዎች ዐዋጅ ቁጥር 678/2002 (በዐዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሻሻለው)፣ የማዕድን ሥራዎች የሚስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 እና የማዕድን ሥዎች መመሪዎችን ያካትታል፤

የኢፌዴሪ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

3. "የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ግምገማ ውጤት አጣሪ ኮሚቴ" /ከዚህ በኋላ ኮሚቴ እየተባለ የሚገለጸው/ ማለት የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለመስጠት በበላይ አመራር የተመራለትን ሰነድ በማጣራት ለበላይ አመራር የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

## 3. ዓላማ

ይህ የውስጥ አሰራር መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የማዕድን ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ የጋራ ኃላፊነት እና አሳታፊነት ላይ የተመረከዘ እንዲሆን እንዲሁም ፈቃድ ጠያቂዎች ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ፤

2. የማዕድን ልማት በአካባቢና በኅብረተሰቡ ላይ ጉዳት ሳያደርስ እና የኅብረተሰቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ እንዲለማ ለማድረግ፣

3. የመንግሥትና የሕዝብ የሆነው የማዕድን ሀብት የበለጠ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊሰጥ በሚችል መልክና ዘለቄታ ባለው ሁኔታ እንዲለማ ለማድረግ ነው።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የውስጥ አሰራር መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚሰጡ የማዕድን ሥራዎች ፈቃዶች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## 5. የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ማመልከቻዎች የሚስተናገዱበት ሂደት

1. የአካባቢና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ መደረጉንና ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ማረጋገጫ መግለጫ ይቀርባል፤

2. በአመልካቾች የሚቀርቡ የሥራ ዕቅዶች በማዕድን ሕጉ፣ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በተዘጋጁ መስፈርቶችና ቅጾች መሠረት ስለመሆኑ በማዕድን ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባለሙያ በጥንቃቄ ተገምግሞ እና ተጣርቶ የግምገማው ውጤት ለኬዝ ቲም አስተባባሪ ይቀርባል፤( የመመዘኛ መስፈርቱ ተያይዟል)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

3. በባለሙያ ተገምግሞ የቀረበው የግምገማ ውጤት በኬዝ ቲም አስተባባሪ በዝርዝር ተፈትሾና ተጣርቶ ለሥራ ክፍሉ ኃላፊ ይቀርባል፤( የመመዘኛ መስፈርቱ ተያይዟል)

4. የሥራ ክፍሉ ኃላፊ በኬዝ ቲም አስተባባሪ በዝርዝር ተጣርቶ የቀረበለትን በማረጋገጥ በግምገማ ሥራ ወቅት የተሟሉትን በመለየት ለንጽጽር በሚያመች ቅጽ በመሙላት ከአመልካቾች ሰነድ ጋር በማያያዝ የፈቃድ ጥያቄው እንዲስተናገድ የውሳኔ ሀሳብ ከማስታወሻ ጋር አያይዞ ለበላይ አመራር ያቀርባል፤( የመመዘኛ መስፈርቱ ተያይዟል)

5. የበላይ አመራሩ ከሥራ ክፍሉ የቀረበለትን ማስታወሻ በማያያዝ ተጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ለኮሚቴው ይመራል፤

## 6. የኮሚቴው አባላት፣ ተግባርና ኃላፊነት

የኮሚቴው አባላት በበላይ አመራር የሚሰየሙ ሲሆን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

| | |
|---|---|
| የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የሚኒስትር አማካሪ | ሰብሳቢ |
| የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የሚኒስትር አማካሪ | አባል |
| የማዕድን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ | አባል |
| የማዕድን ኢንዱስትሪ ግልጽነት ኢኒሼቲቭ ማስፈጸሚያ ጽ/ቤት ኃላፊ | አባል |
| የህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | አባል |
| የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | አባል |
| የማዕድን ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | አስረጅ |
| የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | ፀሐፊ |

## 7. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው በበላይ አመራር በኩል የተላከለትን ዝርዝር የግምገማ ውጤት ከዚህ በታች በተገለጹት የማጣሪያ መመዘኛዎች (Checklist) መሠረት መገምገማቸውን በማጣራት ለበላይ አመራር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## 7.1 ለምርመራ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን፡-

I. የኩባንያው መግለጫ ተጣርቶ መቅረቡን፤

II. የሥራ ዕቅድ መቅረቡን፣

III. ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ በሌላ ባለፈቃድ አለመያዙን የሚያረጋግጥ በካዳስተር የተመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፤

IV. ለሥራው የተመደበው ወጪ ቢያንስ የመጀመሪያውን ዓመት ሥራ ለማሰራት በቂ መሆኑን፤

V. በጋዜጣ መውጣቱና ተቃውሞ ያልቀረበበት መሆኑ.

VI. የፈቃድ ማመልከቻ የሚቀርብበት ቦታ በሚመለከተው ክልል ፈቃድ ያልተሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ መረጃ፣

VII. ፈቃድ የተጠየቀበት የማዕድን ሥራ በዘላቂ የልማት መርህ አግባብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ መደረጉንና ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ማረጋገጫ መግለጫ መቅረቡን፤

VIII. ረቂቅ የምርመራ ፈቃድ ሰነድ መያያዙን፣

IX. እንደ ማዕድኑ ዓይነት ፈቃድ የተጠየቀበት የቦታ ስፋት በሕጉ መሠረት መሆኑን፤

X. በተቀመጠው መስፈርት መሠረት 75 ከመቶ እና በላይ ውጤት ያገኙ መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣

XI. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች በአንድ ቦታ ላይ ለአንድ ዓይነት ማዕድን አንድ ማመልከቻ ለክልል ሌላ ማመልከቻ ደግሞ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ካቀረቡ እና በካዳስተር ሲስተም ተመዝግቦ ከታየ ሚኒስቴሩ እና ክልሉ በጋራ የተስማሙበት መግለጫ መቅረቡን፣

XII. የሚቀርበው የደለል ወርቅ የምርመራ የሥራ ፕሮግራም የፊዚቢሊቲ ጥናትን ጨምሮ ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ጊዜ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ መቅረቡን፣



መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## 7.2 የምርመራ ፈቃድን ለማደስ የሚቀርብ ማመልካቻ ሲሆን፡-

I. የምርመራ ሥራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃድ ዘመኑ ከመፈጸሙ ከ60 (ስልሳ) ቀናት በፊት ጥያቄው የቀረበ መሆኑ፣

II. በማዕድን ሥራዎች አዋጅና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት እና ባለፈው የምርመራ ፈቃድ ዘመን ባለፈቃዱ በውሉና በህግ የተመለከቱትን ግዴታዎች የተወጣ ስለመሆኑ በሥራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፣

III. ማሟላት የሚገባው ዝርዝር መረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸው እና ማቅረብ የሚገባው ሪፖርቶች ቀርበው በሥራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፣

IV. በአዋጁና በደንቡ መሠረት ከምርመራ ፈቃድ ክልሉ ላይ የሚለቀውን መሬት በመቀነስ ዕድሳት የጠየቀበትን ቦታ የሚያመላክት የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔት የያዘ መረጃ መቅረቡን፣

V. ባለፈው የምርመራ ወቅት የተሠሩ ስራዎችና የሚታደስበት ዘመን የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ቀርቦ ይሁንታ ማግኘቱን የሚገልጽ መግለጫ፣

## 7.3 ለምርት ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን፡-

I. ፈቃድ የተጠየቀበት ማመልከቻ ከነ አዋጭነት ሰነድ

II. የኩባንያው መግለጫ ተጣርቶ መቅረቡን፤

III. ከሥራ ክፍሉ የቀረበ የአዋጭነት ጥቅል መግለጫ፣

IV. ፈቃድ የተጠየቀበት የማዕድን ሥራ በዘላቂ የልማት መርህ አግባብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተሟላ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ መካሄዱንና ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ መግለጫ፣

V. እንደ ማዕድኑ ዓይነት ፈቃድ የተጠየቀበት የቦታ ስፋት በሕጉ መሠረት መሆኑን፤

VI. ለፈቃድ ጠያቂው የሚቀርብ በህግ ጉዳዮች የሥራ ክፍል የተዘጋጀ ረቂቅ የስምምነት ሰነድ፣

VII. ባለፈቃዱ በማዕድን ህጉ እና በስምምነቱ መሠረት በምርመራ ፈቃድ ወቅት የገባቸውን ግዴታዎች የተወጣ መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣



የኢፌዴሪ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## 7.4 የምርት ፈቃድን ለማደስ የሚቀርብ ማመልካቻ ሲሆን፡-

I. የልዩ አነስተኛ፣የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃድ ዘመኑ ከመፈጸሙ ከ180 (አንድ መቶ ሰማኒያ) ቀናት በፊት ጥያቄው የቀረበ መሆኑ፣

II. በማዕድን ሥራዎች አዋጅና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት እና ባለፈው የማምረት ፈቃድ ዘመን ባለፈቃዱ በውሉና በህግ የተመለከቱትን ግዴታዎች የተወጣ ስለመሆኑ በሥራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፣

III. ባለፈው የማምረት ፈቃድ ዘመን ማቅረብ የሚገባው ሪፖርቶች ቀርበው በሥራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፣

IV. ባለፈው የማምረት ፈቃድ ዘመን ማሟላት የሚገባው ዝርዝር መረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸው እና በሥራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፣

V. የአካባቢ ኦዲትና የታደሰበት ዘመን የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ቀርቦ ይሁንታ ማግኘቱን የሚገልጽ መግለጫ፣

VI. የአካባቢ ኦዲትና ፈቃዱ ለሚታደስበት ዘመን የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ቀርቦ ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ መግለጫ፣

VII. አመልካቹ የደለል ወርቅ የምርመራ ፈቃዱን ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ በሳው አንድ ወር መጨረሻ የምርመራ ሥራ ክንውን ሪፖርት እና የፊዚቢሊቲ ጥናት ሪፖርት ያቀረበ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፣

## 7.5 ይዞ ለመቆየት የሚቀርብ ማመልካቻ ሲሆን፡-

I. ክምችቱን ወደ ምርት ለማሸጋገር ያልተቻለበትን ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎች ተያይዘው መቅረባቸውን፣

II. ክምችቱን ወደ ምርት ለማሸጋገር ያልተቻለበትን ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎች ተገምግመው መግለጫ መቅረቡን፣



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

## 7.6 ፈቃድን ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማመልካቻ ሲሆን፦

I. የዝውውር ፈቃዱ እንዲተላለፍ ለማስፈቀድ የቀረበ ማመልከቻ ኮፒ፣

II. ፈቃዱን ለማስተላለፍ የተደረገ የስምምነት ውል በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ መቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፣

III. ፈቃድ የሚተላለፍለት ሰው በማዕድን ህጉ መሠረት የተፈቀደለት ሰው ስለመሆኑ ተረጋግጦ መግለጫ መቅረቡን፣

IV. በገቢ ግብር ህግ መሠረት በአስተላላፊው የአክሲዮን ዋጋ ላይ ከሚገኘው ትርፍ ላይ ተገቢው የትርፍ ድርሻ ግብር ስለመፈጸሙ ከገቢዎች ሚኒስቴር መቅረቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

V. ባለፈቃዱ በማዕድን ህጉ እና በስምምነቱ መሠረት ግዴታዎቹን የተወጣ መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

VI. ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በማዕድን ሥራዎች ህግ የፈቃድ ስምምነቶችና አግባብ ያለውን የሥራ ፕሮግራም በፈቃድ አስተላላፊው የተገቡትን ግዴታዎች አክብሮ ለመፈጸም ግዴታ መግባቱን የሚያረጋግጥ መግለጫ፣

VII. ፈቃድ እንዲተላለፍለት የተጠየቀለት ሰው ያቀረባቸው ህጋዊ ሰነዶች እና የሥራ ፕሮግራም/የአዋጪነት ጥናት ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፣

VIII. ፈቃድ እንዲተላለፍለት የተጠየቀለት ሰው የማዕድን ሥራው በዘላቂ የልማት መርህ አግባብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተሟላ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ መካሄዱንና ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ መግለጫ፣

## 8. <u>የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. የኮሚቴው የስብሰባ ቀንና ሰዓት በኮሚቴው አባላት ይወሰናል፣
2. ከበላይ አመራር የፈቃድ ግምገማ ውጤት ለኮሚቴው እንደተላከ የኮሚቴው ሰብሳቢ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ስብሰባ ይጠራል።
3. የኮሚቴው አብላጫ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።



መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

4. ማናቸውም የውሳኔ ሀሳቦች በድምጽ ብልጫ የሚያልፉ ሲሆን በአስረጅነትና በሀሊፊነት የሚመደቡት አባላት ድምጽ አይኖራቸውም፤ ድምጽ እኩል በሆነ ጊዜ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

## 9. የውሳኔ ሀሳብ

1. ኮሚቴው በበላይ አመራር የቀረበለትን የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ግምገማ ውጤትን በማጣራት በአምስት /5/ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡን ለበላይ አመራር ማቅረብ አለበት፤
2. በተራ ቁጥር 1 የተገለጸው ለበላይ አመራር የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በኮሚቴው አባላት የተፈረመ ቃለ ጉባዔ መሆን አለበት፤

## 10. የተሻረ መመሪያ

የማዕድን ምርመራ ጥያቄ ማመልከቻዎች የሚስተናገዱበትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2007 ተሸሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 11. መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ የውስጥ አሰራር መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፤

## ማስታወሻ

ኮሚቴው የቀረበለት ሰነድ ያልተሟላ ነው ብሎ ሲያምን ከአምስት /5/ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መረጃዎችን አሟልቶ እንዲያቀርብ የሥራ ክፍሉን ሊጠይቅ ይችላል፤

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስለግምገማው ውጤት ኮሚቴው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራሮች ቀርቦ ያስረዳል፡፡

መጋቢት 04 2011 ዓ.ም

የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

Company name:

Mineral Type:

Location: -------- National Regional State, --------------- Zone, -----------------Woreda, ----------------- locality.

## Evaluation Criteria for Exploration License Applications

### PART I

| S/N | | Ref. Wt. | Act. Wt | Remark |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Experience and technical capacity | 30 | | |
| 1.1 | No. of years the applicant has been in mining operation and directly/indirectly related experience (max. 5 points) | 5 | | |
| 1.1.1 | Directly related and > 9 years | 5 | | |
| 1.1.2 | Directly related and > 5 - 9 years | 4 | | |
| 1.1.3 | Directly related and 3 - 5 years | 3 | | |
| 1.1.4 | Indirectly related and > 9 years | 3 | | |
| 1.1.5 | Indirectly related and > 5 – 9 years | 2 | | |
| 1.1.6 | Indirectly related and 3 - 5 years | 1 | | |
| | No. of years individual applicant has been in mining operation and directly/indirectly related experience (max.5 points) | 5 | | |
| 1.1.1 | Directly related and > 9 years | 5 | | |
| 1.1.2 | Directly related and > 5 - 9 years | 4 | | |
| 1.1.3 | Directly related and 3 - 5 years | 3 | | |
| 1.1.4 | Indirectly related and > 9 years | 3 | | |
| 1.1.5 | Indirectly related and > 5 – 9 years | 2 | | |
| 1.1.6 | Indirectly related and 3 - 5 years | 1 | | |
| 1.2 | HR capacity & experience (max. 20 points) | 20 | | |
| | o Background of key executives | | | |
| 1.2.1 | Relevant educational background with | 9 | | |
| | · Ph.D | 9 | | |
| | · MSc. , | 8 | | |
| | · BSc. , | 7 | | |
| 1.2.2 | Relevant Experience | 11 | | |
| | · > 10 years | 11 | | |
| | · > 5 - 10 years | 9 | | |
| | · < 5 years | 7 | | |
| 1.3 | Financial performance (max. 5 points) | 5 | | |
| 1.3.1 | Experience of operating in a similar amount of finance with the project under application | | | |
| | § > 75 % of finance under application | 5 | | |
| | § < 75 % of finance under application | 3 | | |
| | *Part I Score* | 30 | | |

### PART II

| S/N | | Ref. Wt. | Act. Wt | Remark |
|---|---|---|---|---|
| 2 | Proposed project location and area coverage(max. 2 points) | 2 | | |
| 2.1 | The area should have coordinate showing lat/long or UTM | 0.5 | | |
| 2.2 | Appropriate projection and datum | 0.5 | | |
| 2.3 | Area coverage should be quantified | 0.5 | | |
| 2.4 | Location map of the area overlain on any geosciences map as base map | 0.5 | | |
| 3 | Objective of the proposed project in specific, measurable, achievable and time framed (SMART) (max. 3 points) | 3 | | |
| 3.1 | Clear objective that can be achieved in long term | 1 | | |



RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3.2 | Clear objective that can be achieved in short term | 2 | | |
| 4 | Previous work assessment citing appropriate reference | 10 | | |
| 4.1 | Chronological literature review of previous works with reference | 3 | | |
| 4.2 | Clear statement about the implication of the assessment in selecting the area | 4 | | |
| 4.3 | Clear statement how the previous work assessment is used in planning the next stage of proposed work | 3 | | |
| 5 | Exploration work proposal (detail exploration program for the 1st year and comprehensive work | 30 | | |
| 5.1 | Exploration work for 1st year | 25 | | |
| 5.1.1 | Appropriate methods (conventional and modern) of exploration (geology, geochemistry, remote sensing, airborne & ground geophysical survey, pitting/trenching, drilling) | 10 | | |
| 5.1.2 | Exploration stage or scale of operation (reconnaissance, regional, follow up, detail, grid system) | 8 | | |
| 5.1.3 | Quantified volume of work with unit of measurement | 5 | | |
| 5.1.4 | Implementation schedule for the 1st year using Gantt chart | 2 | | |
| 5.2 | Comprehensive exploration work for 2nd and 3rd years | 5 | | |
| 6 | Expenditure obligation for the initial three years of exploration period | 10 | | |
| 6.1 | Detail estimated expenditure based on the proposed work program for 1st year | 8 | | |
| 6.1.1 | Required for each human resource | 4 | | |
| 6.1.2 | Required for each equipment and machinery | 2 | | |
| 6.1.3 | Required for each service | 2 | | |
| 6.2 | Comprehensive expenditure for 2nd and 3rd years | 2 | | |
| 7 | Financial status of the applicant related to the exploration period | 15 | | |
| 7.1 | Deposit equal to the minimum of 1st year financial expenditure | 6 | | |
| 7.2 | Equivalent deposit to the minimum of 3 years financial expenditure | 9 | | |
| | *Part II Score* | 70 | | |
| | | | | |
| | *Total Score* | 100 | | |

RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum